# ብሆንማ ኖሮ!!

ከዘለዳው

የውጭ አካል መስሎ፣ ውስጡን ድብልቅልቁን አውጥቶ ገልብጦ፣

ከዘር ዘር ሀረጋት፣ ስቦ እንዳልወረደ፣ እንዳልኖረ አጊጦ፣

ለምውት ስጋዬ፣ ለነባቢት ነፍሴ፣ ነገረው ለራሴ የሆነውን መርጦ።

ባሹቁ በጥሬው፣ እንዳልተቆዘረ፣

ምንም እንዳላየ፣ ጠግቦ እንዳላደረ።

ለካስ አንጀት ባዕድ ነው፣ ሩህሩህ ተብሎ በወሬ በአፍ፣

ካፈቀረው ጋራ፣ ከወደደው ጋራ፣ አንድ አርጎ የማያልፍ።

አካል ስጋ ፈራሽ፣ አሮስቶ ቢለምድ፣ ለቀቅ ባለው ዘመን፣

ያ የጠፋ ለታ፣ ይሆናል ጥምንምን።

ሽምብራ ቢያርበት፣ በገሀድ ተውኔቱ፣

ባቄላ ያሾቃል፣ በልሙ በቅዠቱ።

ጨካኝ አረመኔ፣ ሆኖ ከውስጥ አንጀት፣

በሆዱ ይኩራራል፣ በሚታየው ቀፈት።

ሩህሩህ መባሉን፣ ሳያፍር በራሱ፣

ሁሌ ያሳብባል፣ በተቀፈተተው፣ በጠገበው ከርሱ።

በወሬ ወፍጮ ላይ፣ ቃላትን ገርዳፊ፣

በችግር መከራ፣ ከዓይን እይታ ጠፊ።

በርካታ አንጀቶች፣ ታይተዋል ባለም ላይ፣

ምንታይ  እንታይ ባዮች፣ ወደ ላይ ወደ ላይ።

ብሆንማ ኖሮ፣ ሀይሉ ገሞራውን፣

ብሆንማ ኖሮ፣ ያ ፀገየ ወይን፣

ብዕሬን አንስቼ፣ ባሩዱን ሞልቼ፣ አዘብጠው ነበረ በቀለህ ወያኔን።

ስላልሆንኩ አልሆነም፣ ታየ ባዶነቴ፣

አርበኛ እየቀበርኩ፣ ከባንዳ ሙብላቴ።

ተነሳ ፀጋዬ! ተነሳ ገሞራው!

ማን ይናገርለት፣ ህፃን ምን አፍ አለው?

ዛሬም እንደገና "ዋይ ዋይ" ተዘፈነ፣

ምስሉ በፎቶ ላይ፣ በእንባ ተበተነ።

ብሆንማ ኖሮ! እኒያን ወጣት ጀግኖች!

ለጋ ታዳጊዎች፣

እንደጋዳፊ አይቀርም ጥፊ! ብዬ እዘምር ነበር፣

ኢጋንንት ወያኔን፣ ይኸን የህዝብ ፀር

በድኙ በከርቤው፣ አፍኜ ላባርር።

ብሆንማ ኖሮ እነዛን ጀግኖች፣ እማልሰራው ነገር ምን ይኖር ነበረ፥

ባለመሆኔ እንጂ! ነው አንጀቴ ያረረ።

እንደ እነ ጥላሁን፣ እንደ አበራሽ በርታ፣

ወይ እንደዋለልኝ፣ ወይንም እንደማርታ፣

እንደነ ኢያሱ፣ ሰማየ ሰማያት ሰንጥቄ አየሩን፣

አልተኛም ነበረ፣ ላገር ለወገኔ ቤዛ ለመሆን።

ታዲያ! አለሆንኩምና፣ ተነሳ ፀጋዬ! ተነሳ ገሞራው!

ማን ይናገርለት፣ ህፃን ምን አፍ አለው?

እናንተ ጀግኖቼ፣ ለውጡን ለመመልከት ህይወት የሰጣችሁ፣

ተነሱ አላለቀም ገና ነው ትግላችሁ።

ብሆንማ ኖሮ! ቆስቋሽ መንኮራኩር፣

የጀመራችሁትን፣ ዋናውን ተግባር፣

በዋዛ ፈዛዛ፣ አላልፈውም ነበር።

ህፃናት ሲሞቱ፣ ህዝብ በርሃብ ሲያልቅ፣

እያየሁኝ ባይኔ፣ ምን ሲሆን ልንፏቀቅ?

ብሆንማ ኖሮ! እነኛን ጀግኖቼ፣

የመለስን ጣኦት፣ ከመሬት አውጥቼ፣

ፍርድ አሰጠው ነበር፣ ተርቦ በሚያልቀው፣

ከኖረበት ቀዬ፣ ከሚገፈተረው፣

ሆኖም ስላይደለሁ፣ ተነሳ ሎሬት! ተነሳ ተስፋዬ!

ተነሱ እናንት ጀግኖች!

ሀገረ ኢትዮጵያ መሸቀያ ሆነች።

ብሆንማ ኖሮ!

ብሆንማ ኖሮ ......................

//////////////////---------------//////////////////